# "የማውቀው የለኝም "-- ማን ሊያምንህ ትለፋለህ ገብሩ አስራት!

ከመዝገቡ ባየህ

የአቶ መለስ ዜናዊ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው የቀድሞ የወያኔ መሪ ገብሩ አስራት በላስ ቬጋስ ባለፈው ሰሞን ባደረገው ስብሰባ ላይ በወያኔ ተይዘው ደብዛቸው ስለጠፋው ስለነ ጸጋዬ ገብረ መድህን ሲጠየቅ በመሰረቱ የማውቀው የለኝምን መልስ ስጥቶ አልፏል። በጦርነት ወቅትም ሞተዋል ሲባልም ሰምቻለሁ ብሎ ተናግሯል።

በመጀመሪያ ደረጃ ይህ እነ ጸጋዬ በውጊያ ጊዜ ሞተዋል እየተባለ በወያኔዎች አልፎ አልፎ የሚወራው ፍጹም ሀሰት መሆኑ ሊጋለጥ ይገባዋል። ጸጋዬና ጓዶቹ ባሕርዳር እስር ቤት ሳሉ ብዙ ታስረው የተፈቱ የኢሕአፓ አባላት አይተዋቸዋል። ከዚያ ወዲያ ወደ ትግራይ ተወሰዱ ሲባል፤ በዚያውና ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ደብዛቸው ጠፍቷል። በዚያን ወቅት አቶ ገብሩ የወያኔ ድርጅት ፖሊት ቢሮ አባልና የትግራይ ፕሬዚዴንት ነበር። በነ ጸጋዬ ላይ የተወሰነውን እሱም ሆነ እነ ስዬ፣ ተወልደና አለምሰገድ አያውቁም ነበር ማለት ያስቸግራል። በተደጋጋሚ የሚናፈሰው ወሬ የነ ጸጋዬን በትግራይ መገደል ይጠቅሳል። ይህ እውነት ከሆነ እነ ገብሩ የወንጀሉ ተባባሪና ተጠያቂም ናቸው። ይህንንም ማመን ይጠበቅባቸዋል። እየካዱና አናውቅም እያሉ ሕዝብን እመነኝ ማለቱ የሚያዋጣ አይደለም፣ አይሆንም።

እነ ጸጋዬም የደረሱበትን ማወቅ የሚሹ፣ በትውስታ ሰቀቀን እየባነኑ የሚኖሩ ዘመድ አዝማዶች አሏቸው። እነ ጸጋዬም የደረሱበትን ማወቅ የሚሹ፣ ትውስታቸውን የሰቀቀናቸው ስንቅ አድርገው የሚኖሩ ወዳጆች አሏቸው። እነ ጸጋዬም የደረሱበትን ማወቅ የሚሹ፣ በትውስታ ሰቀቀን እየተብከነከኑ የሚኖሩ፣ ደርግንም ሆነ አሁን የአገዛዙን ወንበር የተቆናጠጡትን ወይም ይህንኑ ለማስቀጠል በእጅ አዙር የመጡትን ወያኔዎች ሲታገሉ የነበሩበትን ክቡር ዓላማ አንግበው ትግሉን የቀጠሉ ጓዶች አሏቸው - ከኢትዮጵያ ሕዝብ ወግነው።

እንኳን ሰውና ሌላው እንሰሳም ከጎኑ በጅብ የተበላ ጓዱን ፍፁም ስለመርሳቱና ከዚያው በላተኛ ጅብ ጋር የማይሆን ወዳጅነት ስለመመስረቱ ገና ሳይንሱም አላረጋገጠ። የጅብን ጩኸት የጅብ ጩኸት ብሎ እንጂ በሌላ አይተረጉመውም። የነ ገብሩ የእመኑን ጩኸትም እንደዚያው ነው። የሕዝብን ልጆች መዳረሻ ሳይናገሩ፣ በጸረ-

ኢትዮጵያ የአገዛዝ መጋዛቸው በበኋቸው፣ በትግራይም ሆነ በሌላው የሐገራችን ክፍል በከፈቷቸው የጨለማ እስር ቤቶች ያጎሯቸውን ታጋይ የኢትዮጵያ ልጆች ሁኔታ ለሕዝብ ሳያሳውቁ ከሕዝባዊ ትግል ጎራ ሊቀላቀሉ አይገባም። ትላንት ለጋራ ለቆምንላቸው ለኢትዮጵያ እና ሕዝቧ ሲታገሉ ከጎናችን ስለወደቁት ወይም ተይዘው መዳረሻቸው ስለጠፋው መጠየቅን እየረሳን፣ ከገዳዮቻቸው እና ካሳሪዎቻቸው ጋር ታንጎ የምንደንስ ከሆነ የቱ ላይ ነው ጽናታችን ? የቱ ላይ ነው ለመርህ ታማኝነታችን ? የምንታገልለት የሰብአዊ መብት ጥያቄስ እነኛን ዛሬ ከጎናችን የሌሉትን የሕዝብ ልጆች አያካትትም እንዴ ? « ለፋሲካ እርድ የተተዎ በግ ለገና በታረደው በግ አፌዘ » እንዲሉ እየሆነ ነው አንዳንዶቻችን። በድረ-ገፆች ላይ የሚወጡ አንዳንድ ጽሑፎች የሚያስደምሙ ናቸው። ከሰሞኑ የነስዬን አሸሸ ገዳሜ ከበሮ ድለቃ የተቀላቀሉት አቶ እስክንድር ነጋ «The past of Seye Abraha et al in perspective » በሚል ርዕስ፣ ኢትዮሚዲያ ላይ በ April 16, 2010 ባወጡት ጽሁፍ እንዲህ ብለዋል - ወደ አማርኛ ሲመለስ፡

« ዋናው ቁም ነገር፣ ከደርግ የአገዛዝ ዘመን በተያያዘ ያለርህራሄ ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ታስሮ እጁ ተሰጥቶ እድሜ ይፍታህ በተፈረደበት ቀልቤሳ ነገዎ ላይ እንደቀረበው፣ በስዬ አብርሃና ሌሎቹም ላይ በማስረጃ የተደገፈና በግልጽ የተቀመጠ የሰብአዊ ጥሰት ስለማድረጋቸው ጥያቄ አልቀረበባቸውም። ነገር ግን መጠነ ሰፊ የሆነ የሰብአዊ መበት ጥሰትን ጨምሮ እጅግ የበዛ እንከን ያለበትን አገዛዝ በማገልገላቸው ይወገዛሉ። ሆኖም ግን ሁሉም ማለት ይቻላል በተለያየ ጊዜ ይህን ጉዳይ አንስተው ተናግረዋል፣ ለሕዝብም ጸጸታቸውን ገልጸዋል። አሁንም የቀድሞ ፓርቲያቸውን እየታገሉት ነው። »

የትርጉም ስህተት ከፈጸምኩ ደግሞ እንግሊዝኛው ኦሪጂናል እንደሚከተለው ይነበባል፡

« … Of crucial point here is that none amongst Seye Abraha et al is being asked to account for substantiated and specific violation of human rights, as was the case, for example, with Kelbessa Negawo from the Derg era, who was unsympathetically deported from the US to Ethiopia to serve a life sentence; but are being decried for serving a regime with broad shortcomings, including of course extensive human rights violation. But almost all of them have at one time or the other addressed the issue, publicly expressed regret and are now challenging their former party at the height of its power… »

ለመሆኑ ስለማን አገዳደል ነው የተናገሩት? ለመሆኑ እነማን በምን ሁኔታ የት እንደተገደሉ ወይም እንደታሰሩ ነው የተናገሩት? ለመሆኑ በማን እና እንዴት ምን ዓይነት ብሄራዊ ወንጀል እንደተሰራ ነው የተናገሩት? ከየትኛው ሀገር ወይም የውጪ ተቋም ጋር በየትኛው የሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ላይ እንደተደራደሩና አሳልፈው እንደሰጡ ነው የነገሩን? እነሱ ያላሉትን አሉ ብንልስ፣ እውነት ከበሬታን ከእነሱ እናተርፋለን ብለን እናስባለን? አሁን ከመለስ ጋር በስልጣን በመጣላታቸው፣ አብረው ሲገዙን በነበረ ጊዜ ለተፈጸመው ጸረ-ኢትዮጵና ጸረ-ህዝብ ድርጊት መለስን ብቻ ተጠያቂ ለማድረግ በሚሞክሩበት ታንጎ መደነሱስ አያሳፍርም? ማነው የትግራይ ሕዝብ ስራ አለበት፣ ጋዜጣ ለማንበብ ብሎ ህዝብ በግንባር ቀደምነት ሲያፍን የነበረው? ማነው እነ ጸጋዬ የታሰሩባቸው ድብቅ እስር ቤቶች የሚገኙበትን ትግራይን ይገዛ የነበረው? በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ በጎንደር ወዘተ የሰላማዊ ዜጎቻችን ደም በጭካኔ ሲፈስ ማን ነበር « ጦርነት መስራት እንችላለን ! » ብሎ እየፎገላ ጦር አዛዥ የነበረው? ለመሆኑ እነ ስዬ የሰብአዊ መብት ጥሰት ወንጀል ስለማድረጋቸው ለማወቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስክር ያስፈልገዋል? ትላንትም ዛሬም እኮ የወንጀሉ ገፈት ቀማሽ ሕዝቡ ነው። ሕዝብን መናቅ ጥሩ አይደለም። ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ የሚለውን ምሳሌ ማስታወሱ ጥሩ ሳይሆን አይቀርም። አለዚያማ ሕዝባችን በስነ-ቃሉ እንዲህ ብሏል፡

ጠላትማ አንድ ጊዜ ጠላት ነው፣
አስቀድሞ መግደል፣ አሾክሿኪውን ነው።

ልብ ይስጠን።